የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ–የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 17
ADDIS ABABA - 19th Feb., 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፺፰/፲፱፻፺ ዓ.ም.
ስለንግድ ተቋም የዋስትና መያዣ የወጣ
አዋጅ ........................................................ ገጽ ፮፻፸፯

## CONTENTS

Proclamation No.98/1998
A Proclamation to Provide for Business Mortgage
Proclamation ........................................... Page 677
Corrigendum No. 1/1998 ......................... Page 681

## አዋጅ ቁጥር ፺፰/፲፱፻፺

## ስለንግድ ተቋም የዋስትና መያዣ የወጣ አዋጅ

የንግድ ተቋሞች በዋስትና መያዣነት ስለሚመዘገቡበት መዝገቦች አያያዝና አፈጻጸም ፣ ዋስትናውን ከመዝገብ ስለመሰረዝና ስለሥርዓቱ በሕግ እንደሚደነገግ በንግድ ሕጉ አንቀጽ ፩፻፹፮ የተመለከተ በመሆኑ ፣

በንግድ ሕጉ አንቀጽ ፩፻፸፱ በንግድ ተቋም ላይ የሚሠጡ መያዣዎችን ስለማስመዝገብ የተመለከቱት ድንጋጌዎች የሚጸኑት ወደፊት በነጋሪት ጋዜጣ በሚነገረው ቀንና ሁኔታ መሠረት እንደሚሆን በዚሁ የንግድ ሕግ አንቀጽ ፩ሺ.፩፻፸፭(፩) የተደነገገ በመሆኑ ፤

ለኢኮኖሚው እንቅስቃሴ አመች ሁኔታ ለመፍጠር የንግድ ተቋሞቻቸውን ለባንክ በዋስትና ካስያዙ ባለዕዳዎች ላይ የሚፈለጉ ዕዳዎችን በተቀላጠፈ መንገድ ማሰባሰብና ለወደፊቱ ጥሩ የንግድ አሠራር ባሕል እንዲዳብር ማድረግ በማስፈለጉ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

## PROCLAMATION NO.98/1998

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR BUSINESS MORTGAGE

WHEREAS, it is stated under Article 186 of the Commercial Code that the manner of keeping register of mortgage of business and canceling entries shall be specified by law;

WHEREAS, it is also stated under Article 1175(1) of the Commercial Code that the provisions of Article 179 of the Code relating to registration of Commercial Mortgage shall come into force on such day and on such conditions as shall be notified by order published in the Negarit Gazeta;

WHEREAS, in order to create conducive environment to the economic development by enabling banks to efficiently collect debts from debtors whose business has been mortgaged with the banks and thereby establishing a good business culture;

NOW,THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ስለንግድ ተቋም የዋስትና መያዣ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፺፰/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩. "የንግድ ተቋም" ማለት በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. በወጣው የንግድ ሕግ የተመለከተው የንግድ መደብር ነው፣

፪. "ቢሮ" ማለት የክልል ወይም የከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ወይም በዋስትና የተሰጡ መያዣዎችን እንዲመዘግብ ሥልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አካል ነው፤

፫. "ከተማ" ማለት አዲስ አበባ ፡ ድሬዳዋ ወይም ሌላ ለፌዴራሉ መንግሥት ተጠሪ የሆነ ከተማ ነው ፤

፬. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፵፯ ውስጥ የተመለከተ ክልል ነው ፡

፭. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለንግድ ተቋም ዋስትና መያዣ ምዝገባ

፫. መዝገብ ስለማቋቋም

፩. በንግድ ተቋም ላይ የሚደረግ የዋስትና መያዣ መዝገብ በያንዳንዱ ክልል ወይም ከተማ ይቋቋማል ፡፡

፪. የዋስትና መያዣ መዝገብ አደረጃጀትና አቀማመጥ በክልል ወይም በከተማ አስፈጻሚ አካል ይወሰናል፡፡

፬. ስለንግድ ፈቃድ አስፈላጊነት

የንግድ ተቋምን በመያዣነት ለመስጠት በቅድሚያ የንግድ ተቋሙ አግባብ ባለው የፌዴራል ወይም የክልል አካል ተመዝግቦ የንግድ ፈቃድ ያወጣ መሆን አለበት ፡፡

፭. ለምዝገባ ስለማመልከት

፩. ማናቸውም የዋስትና መያዣ ጥያቄ ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው አመልካችነት ሊቀርብ ይችላል፡፡

፪. የዋስትና መያዣ ለማስመዝገብ ጥያቄ የሚቀርበው በቢሮው የተዘጋጀውን የምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ በሁለት ኮፒ ሞልቶ በማቅረብ ይሆናል፡፡

፫. አመልካቹ ከቅጹ ጋር ለምዝገባው ጥያቄ መነሻ የሆነውን የውል ሰነድ ወይም ሌላ ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል

፬. ቢሮው ቅጹ ተሞልቶ ሲቀርብለት ትክክለኛነቱን ካረጋገጠ በኋላ እንደአመጣጡ ለቅጹ ተከታታይ ቁጥር ይሰጠዋል፡፡

፮. ስለምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ ይዘት

፩. ቢሮው ለዋስትና መያዣ ምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ አዘጋጅቶ ያወጣል፡፡

፪. የምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ) የምዝገባ ጥያቄ ያቀረበው ሰው ወይም ወኪል ስምና አድራሻ ፡

ለ) የንግድ ተቋሙ አስቀድሞ በመያዣነት የተሰጠ ከሆነ የመዝገቡ ቁጥርና ቀን ፡



## PART ONE
## *General*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as "Business Mortgage Proclamation No. 98/1998."

2. *Definition*

In this Proclamation:

1) "Business" means a business specified under the 1960 Commercial Code of Ethiopia;
2) "Bureau" means Regional or City Bureau of Commerce and Industry or a Regional or City authority entrusted with the power to register mortgages;
3) "City" means Addis Ababa; Dire Dawa or any City which is accountable to the Federal Government;
4) "Region" means a region specified under Art.47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;
5) "Person" means a natural or juridical Person.

## PART TWO
## *Registration of Business Mortgage*

3. *Keeping of Register*

1) Register of mortgage of business shall be kept in each Region or City.
2) The manner of organizing and keeping of register of mortgage shall be determined by the Executive Organ of the Region or City.

4. *Requirement of Business License*

In order to mortgage a business, the business shall be one which has been registered and given business license by the appropriate Federal or Regional authority.

5. *Application for Registration*

1) Any request for registration of mortgage of business may be submitted by the concerned person.
2) The request for registration of mortgage shall be submitted by filling in two copies the application forms for registration prepared by the Bureau.
3) The Applicant shall attach the contract or other evidence which is the basis for the request of registration.
4) When the forms are presented to the Bureau, the Bureau shall, after verifying the forms, give consecutive numbers in the order of their submission.

6. *Content of Application form for Registration*

1) The Bureau shall prepare application form for registration.
2) The application form for registration shall include the following:
   (a) the name and address of the applicant or agent requesting for registration;
   (b) if the business has been mortgaged previously the registry number and date of registry;

ሐ) የዋስትና መያዣው ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መሆኑ፡
መ) የምዝገባው ጥያቄ አዲስ ምዝገባ ለማድረግ ወይም ቀድሞ የተደረገ ምዝገባን ለማሻሻል የቀረበ መሆኑ፡
ሠ) ቅጹ የተሞላበት ቀን ፡ ወር እና ዓመተ ምህረት ።

፯· <u>የንብረት መለያ ምልክት ስለመስጠት</u>

፩· በንግድ ሕጉ አንቀጽ ፻፸፭(፩) (ሰ) እና አንቀጽ ፻፸፱(፩) (ሠ) መሠረት በዋስትና መያዣነት በተሰጡት የንግድ ተቋም ንብረቶች ላይ የዋስትና መያዣ የተሰጠው ገንዘብ ጠያቂ መለያ ምልክት ሊያደርግባቸው ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጡት መለያ ምልክቶች በመዝገብ ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል።

፰· <u>በመዝገብ ስለሚጻፉ መግለጫዎች</u>

፩· በመዝገብ ውስጥ የሚገቡ አስፈላጊ መግለጫዎች፡ በተለይም፡
ሀ) የዋስትና መያዣው በመዝገብ የገባበት ቀን፡ ወርና ዓመተ ምህረት ፡
ለ) ማናቸውም የገንዘብ መጠን ወይም ሌላ ድምር በአኃዝና በፊደል ፡
በማሻያማ ሁኔታ በግልጽ መጻፍ ይኖርባቸዋል ።

፪· በመዝገብ ላይ የሚጻፉ መግለጫዎች በማይጠፉ ቀለም መጻፍ ይኖርባቸዋል።

፱· <u>ስለመመዝገብና ስለምዝገባ ክፍያ</u>

ማንኛውም የዋስትና መያዣ ምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ ከአስፈላጊው ሰነዶች ጋር ቀርቦ የተሟላ መሆኑን ቢሮው ካረጋገጠ አመልካቹን የምዝገባ ክፍያ በማስከፈል ይመዘግባል ።

፲· <u>በመዝገብ የገቡ መግለጫዎችን ስለማረም</u>

፩· በመዝገቡ ውስጥ የገባ ማንኛውም መግለጫ ያልተሟላ ወይም ትክክል ያልሆነ ሆኖ ከተገኘ ሊታረም ይችላል ።

፪· ቢሮው በመዝገብ የገቡ መግለጫዎች ስለሚታረሙበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል።

፲፩· <u>ቁጥጥር ስለማድረግ</u>

ቢሮው በዋስትና መያዣነት የተመዘገበውን የንግድ ተቋም ስለሚገኝበት ሁኔታ ለማጣራት ወይም ለመመርመር በቦታው ተገኝቶ ለመቆጣጠር ወይም መግለጫ እንዲሰጥበት ለመጠየቅ ይችላል ፤ ባለንብረቱም ተገቢውን ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት ።

፲፪· <u>ስለመሰረዝ ሥርዓት</u>

፩· የዋስትና መያዣው ከመዝገብ እንዲሰረዝለት የሚጠይቅ ሰው መያዣው እንዲለቀቅለት የተደረገበትን ስምምነት ወይም በፍርድ ቤት የተሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ ማቅረብ ይኖርበታል ።

፪· መዝጋቢው የቀረበውን ሰነድ ትክክለኛነት በማረጋገጥ መያዣውን ከመዝገብ ይሰርዛል።

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>በዋስትና የተሰጠን የንግድ ተቋም በሐራጅ ስለመሸጥ</u>

፲፫· <u>የዋስትና መያዣ ስምምነት</u>

የ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. የንግድ ሕግ አንቀጽ ፻፹፱ ቢኖርም ፤ የዋስትና መያዣ ያለው ገንዘብ ጠያቂ ባንክ የሚፈልገው ገንዘብ ሳይከፈለው ቢቀር ከሠላሳ ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ ለባለዕዳው በመስጠት ለባንክ ብድር ዋስትና በመያዣ የተሰጠን የንግድ ተቋም በሐራጅ ለመሸጥና የንግድ ተቋሙን የባለቤትነት መብት ለገዢ ለማዛወር ወይም ለሁለተኛ ጊዜ በወጣ የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት ገዢ ካልቀረበ ንብረቱን በብድር ውሉ ውስጥ በሰፈረው የዋጋ ግምት መሠረት ለመውሰድና የባለቤትነት መብቱ በስሙ እንዲዛወርለት ለማድረግ ከባለዕዳ ጋር የሚያደርገው ስምምነት ተፈጻሚነት ይኖረዋል።



(c) whether the mortgage emanates from the law or contract;
(d) whether the application for registration is for making new registration or amending the existing registration;
(e) the day, month and year of the filling of the form.

7. *Identification Marks*

1) The secured creditor may put identification mark on the property mortgaged based on Article 175(1)(g) and Article 179(1)(e) of the Commercial Code.

2) The identification marks made in accordance with sub-Article(1) of this Article shall be entered in the Register.

8. *Information entered in the Register*

1) Important information entered in the register, in particular:
(a) the day, month and year of the entry of the mortgage in the Register;
(b) any amount of money or other sums both in numbers and words;
shall be written clearly.

2) any information entered in the register shall be written in ink which does not fade-out.

9. *Registration and Registration Fee*

If an application form for registration of mortgage with the necessary documents has been presented and verified by the Bureau, the applicant shall pay registration fee.

10. *Correction of Information Entered in the Register*

1) Any information entered in the register, may be corrected if it is found to be incomplete or incorrect.

2) The Bureau shall issue directives regarding correction of information entered in the register,

11. *Inspection*

The Bureau may, in order to investigate or inspect the status of the business registered as a mortgage, inspect the said business on site or request information. The owner has an obligation to cooperate thereto.

12. *Cancellation Procedure*

1) A person who requests for the cancellation of a mortgage from the register shall submit the agreement allowing the release of the mortgage or the final judgement of the court.

2) The registrar shall, after verifying the document submitted to it, cancel the mortgage from the register.

PART THREE

*Selling of Business Mortgage by Auction*

13. *Agreement of Mortgage*

Notwithstanding the provisions of Article 189 of the Commercial Code, an agreement which authorizes a secured creditor bank whose claim is not paid to sell the mortgaged business, by auction upon giving a prior notice of at least 30 days to the debtor, and to transfer the ownership of the business to the buyer or to take over the business, in consideration of its estimated value as specified in the contract of loan, and have the ownership thereof registered in its own name; in cases where bidders fail to appear upon a second public auction having been held shall be valid.

፲፬. <u>በንግድ ተቋም ላይ ያለ የዋስትና መብት</u>

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የንግድ ሕጉ የንግድ ተቋም መያዣ እንዲመዘገብ በማስገደዱ በአንቀጽ ፲፩፻፸፭(፪) መሠረት በአውራጃ ፍርድ ቤት የተመዘገበ የዋስትና መያዣ ያለውና ገንዘቡ ያልተከፈለው ገንዘብ ጠያቂ ባንክ ለባለዕዳው ከሠላሳ ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የንግድ ተቋሙን በሐራጅ ለመሸጥና ባለቤትነቱንም ለገዢው ለማዛወር ወይም ለሁለተኛ ጊዜ በወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት ገዢ ካልቀረበ ንብረቱን በብድር ውሉ ውስጥ በሰፈረው የዋጋ ግምት መሠረት ለመውሰድና የባለቤትነት መብቱ በስሙ እንዲዛወርለት ለማድረግ ይችላል።

፲፭. <u>በባንክና በባለዕዳው መካከል ስለሚኖር ግንኙነት</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ እና ፲፬ መሠረት በባንክ የተደረገ ሽያጭ ባለዕዳውን በመወከል እንደተፈጸመ ይቆጠራል።

፲፮. <u>በሐራጅ ሽያጭ ላይ የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ተፈጻሚ ስለመሆኑ</u>

ባንክ በዋስትና መያዣ የያዘውን የንግድ ተቋም በሐራጅ የመሸጥ ሥልጣኑን በሥራ ላይ በሚያውልበት ጊዜ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ከቁጥር ፫፻፺፬–፬፻፵፱ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል ።

፲፯. <u>ስለባንክ ተጠያቂነት</u>

ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ የተጠቀሱትን አግባብ ያላቸውን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ሽያጩን በመፈጸሙ ባለዕዳው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በኃላፊነት ተጠያቂ ይሆናል።

፲፰. <u>የቢሮው ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

፩. የዋስትና መያዣውን የመዘገበው ቢሮ ለሐራጅ ሽያጭ አፈጻጸም የሚረዱ አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣንና ኃላፊነት አለው ።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ቢሮው ለሚወስደው እርምጃ የፖሊስ ኃይል መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ያገኘው እንደሆነ ፖሊስን ማዘዝ ይችላል።

፲፱. <u>በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ስላሉ ጉዳዮች</u>

የንግድ ተቋምን በዋስትና በያዘ ባለገንዘብ ባንክ አመልካችነት ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያለ ክስ ወይም አፈጻጸም ተቋርጦ በዚህ አዋጅ መሠረት ባንኩ የንግድ ተቋሙን በሐራጅ ለመሸጥና የባለቤትነቱንም መብት ለገዢ ለማስተላለፍ ይችላል ።

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፳. <u>ስለንግድ ሕግ አፈጻጸም</u>

፩. አግባብ ያላቸው የ፲፱፻፶፪ ዓ.ም የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች በንግድ ተቋም የዋስትና መያዣዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

፪. ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም በንግድ ሕጉ የንግድ ተቋምን በዋስትና ማስያዝን በሚመለከቱት ድንጋጌዎች ውስጥ፣

ሀ) ክልልን የሚመለከት ከሆነ "ጠቅላይ ግዛት" የሚለው "ክልል" እንዲሁም "የንግድ ሚኒስቴር" የሚለው "ቢሮ"፣ ወይም

14. *Claim on Mortgaged Business*

A secured creditor bank which, prior to the effective date of this Proclamation, has a claim on business mortgage, registered in the Awraja Court in accordance with Article 1175(2) of the Commercial Code as a result of a legal imposition to register mortgage on a business, may sell the business by auction upon by giving a prior notice of at least 30 days to the debtor and transfer the ownership to the buyer or take over the business, in consideration of its estimated value as specified in the contract of loan, and have the ownership thereof registered in its own name; in cases where bidders fail to appear upon a second public auction having been held.

15. *Relationship between the Bank and the Debtor*

The sale made in accordance with Articles 13 and 14 of this Proclamation shall be deemed to have been executed on behalf of the debtor.

16. *Application of the Civil Procedure Code to Auction*

The provisions of Article 394-449 of the Civil Procedure Code shall, mutatis mutandis, be applicable while the Bank is exercising its power of selling the business mortgage by auction.

17. *Liability of the Bank*

The Bank shall be liable for any damage it causes to the debtor in the process of selling in violation of the relevant provisions of the Civil Procedure Code specified under Article 16 of this Proclamation.

18. *Powers and Duties of the Bureau*

1) The Bureau which has registered the business mortgage shall have the powers and duties to take the necessary measures for carrying out the sale by auction.

2. If the Bureau, while taking action in accordance with sub-Article(1) of this Article, finds it necessary to use police force, it may order police.

19. *Cases Pending before the Court*

Any suit or decree on execution, pending before a court prior to the coming into force of this Proclamation, may be terminated upon application by the creditor bank with which the business has been mortgaged and the bank may sell the business by auction and transfer the property to the buyer in accordance with this Proclamation.

## PART FOUR
## *Miscellaneous Provisions*

20. *Applicability of the Commercial Code*

1) The relevant provisions of the 1960 Commercial Code shall be applicable in mortgage of business.

2. For the purpose of this Proclamation, the provisions in the Commercial Code concerning mortgage of business shall be read as follows:

(a) if it concerns a Region the word "Teklay-gizat" shall be read as "Region" and the "Ministry of Commerce and Industry" shall be read as "Bureau"

ለ) ከተማን የሚመለከት ከሆነ "ጠቅላይ ግዛት" የሚለው "ከተማ" እንዲሁም "ንግድ ሚኒስቴር" የሚለው "ቢሮ" ተብሎ ይነበባል።

፳፩· ስለ ክፍያ

በንግድ ሕጉና በዚህ አዋጅ መሠረት ለዋስትና መያዣ ምዝገባና ለተዛመዱ አገልግሎቶች የሚከፈል ክፍያ በክልል ወይም በከተማ ሕግ ይወሰናል።

፳፪· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

በንግድ ተቋም ላይ ስለሚሰጡ መያዣዎች ምዝገባ የንግድ ሕጉ አንቀጽ ፩፻፸፱ እና የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች የሚጸኑት ከየካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም ጀምሮ ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት



(b) if it concerns City the word "Teklay-gizat" shall be read as "City" and the "Ministry of Commerce and Industry" shall be read as "Bureau".

21. *Fees*

Fees for registration of mortgage and related services based on the Commercial Code and this Porclamation shall be determined by City or Regional law.

22. *Effective Date*

The provisions of Article 179 of the Commercial Code on registration of mortgage and the provisions of this Proclamation shall enter into force as of the 19th day of February, 1998.

Done at Addis Ababa, this 19th day of February, 1998.

NEGASO GIDADA(DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC

REPUBLIC OF EHTIOPIA

Corrigendum No. 1/1998

Property Mortaged or Pledged with Banks Proclamation No. 97/ '1998 is hereby corrected by:

1. omission of the "," after the word "buyer", in Article 3, and insertion thereinafter of the phrase "or to take over the property, in consideration of its estimatd value as specified in the contract of loan, and have the ownership thereof registered in its own name; in cases where bidders fail to appear upon a second public auction having been held."; and
2. omission of the "." at the end, of Article 4, and addition thereinafter of the phrase "or take over the property, in consideration of its estimated value as specified in the contract of loan, and have the ownership thereof registerd in its own name; in cases where bidders fail to appear upon a second public auction having been held.".